# የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ

የአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 353 የካቲት 6 2007 ገጽ 1


ለኢትዮጵያዊ ወታደር ለህወሃት ሎሌ ከመሆን በላይ የሞት ሞት የለም። ብዙሃኑ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊቱ አባላት በጥቂት የወያኔ ሹማምንት የሚረገጡ መሆኑ የሠራዊቱን አባላት የግል ስብዕና ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የሠራዊቱን ክብር ይነካል። የሠራዊታችን የህወሓት አገልጋይ መሆን የምንወዳት አገራችን ኢትዮጵያን ያዋርዳል። ይህ ዉርደት በዚህ ሁኔታ መቀጠል የለበትም።

ከአርበኞች ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## 2007ቱን ሀገራዊ ምርጫ ሂደት እና ከምርጫዉ ዉጭ ያሉ አዋጭ አማራጮችን በተመለከተ የአርበኞች ግንቦት 7: የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ የአቋም መግለጫ

አርበኞች ግንቦት 7: የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላማዊ፣ ተዓማኒና ፍትሀዊ በሆነ ምርጫ የማይፈልጋቸውን መሪዎች መሻር፤ የሚፈልጋቸውን ደግሞ መሾም መሚያስችሉትን መሠረቶች ለመጣል የሚታገል ንቅናቄ ነው። እንደሚታወቀው የሕዝብ እውነተኛ ፍላጎት የሚገለጽበት እውነተኛ ምርጫ እንዲኖር ገለልተኛና ቀልጣፋ የፍትህ ሥርዓት፣ የጦርና የፖሊስ ሠራዊት ሊኖሩ ይገባል። ነፃ የሚዲያ ተቋማትና በነፃነት የሚንቀሳቀሱ የሲቪክ ማኅበራት መኖርም መታለፍ የሌለባቸው አቢይ ጉዳዮች ናቸው። አማራጭ ፓሊሲዎችን ማቅረብ የሚችሉ በነፃነት የሚንቀሳቀሱ የፓለቲካ ፓርቲዎች ከሌሉም አማራጮች የሉምና ምርጫ ትርጉም የለውም። ይህ ሁሉ ቢሟላ እንኳን ምርጫውን የሚያስፈጽመው አካል ገለልተኛ፣ ሀቀኛና ተዓማኒ ካልሆነ የሚደረገው ምርጫ የመራጩን ሕዝብ ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ሊሆን አይችልም።

ከላይ የተዘረዘሩትን የምርጫ እሴቶች ሙሉ በሙሉ ባይሆንም እንኳን የተወሰኑትን በመጠኑም ቢሆን ያካተተ ምርጫ እንዲኖር መጣርና በሂደት የምርጫውን አፈፃፀም ማሻሻል ይቻል ይሆናል በሚል እምነት የዲሞክራሲ ኃይሎች በህወሓት የሴራ ምርጫዎች ሲሳተፉ ቆይተዋል። ሆኖም በህወሓትና በእውነተኛ ምርጫ መካከል ያለው ተቃርኖ እያደር እየሰፋ ሲሄድ እንጂ ሲጠብ አልታየም። በህወሓት ሙሉ ቁጥጥር ስር በሚካሄድ ምርጫ ኢትዮጵያን የሚጠቅም ለውጥ ሊመጣ ይችላል የሚለው እምነት ለአርበኞች ግንቦት 7 ፈጽሞ የተሟጠጠው ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ ነው። በግንቦት 7 ቀን 1997 ዓም የኢትዮጵያ ሕዝብ በታላቅ የለውጥ ተስፋ የሰጠው ድምጽ በህወሓት የተዘረፈው ከላይ የተዘረዘሩት ተቋማት ያልነበሩ በመሆናቸው፤ ስለዚህም ከምርጫ በፊት ተቋማቱን መገንባት፤ ተቋማቱን ለመገንባት ደግሞ ህወሓትን ከስልጣን ማስወገድ ይገባል ብሎ በማመኑ ነው አርበኞች ግንቦት 7 በሁለገብ የትግል ስልት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው።

ያም ሆኖ ግን በምርጫ ላይ ያላቸው ተስፋ ፈጽሞ ያልተሟጠጠ ፓርቲዎችን በማክበርና ሥራቸውንም አስቸጋሪ ላለማድረግ ሲባል ከምርጫ 97 ወዲህ የነበሩ ብሄራዊም ሆነ ክልላዊ ምርጫዎችን አስመልክቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከምርጫ ዉጭ ያሉ ሌሎች አማራጮችን ብቻ እንዲመለከት አርበኞች ግንቦት 7 ጥሪ አድርጎ አያውቅም ነበር። አሁን ግን የአገራችን ኢትዮጵያ የፓለቲካ ሁኔታዎች ይህንን የቆየ አቋም በሚያስቀይር መንገድ፤ የአገራችንን የወደፊት ዕድል ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ ያካባቢውን ሰላም በሚጎዳ መልኩ ተቀይሯል። የሰሞኑ የወያኔ እርምጃዎች ትንሽ ተስፋ ያደርግ የነበረውን የዴሞክራሲ ወገንተኛ ተስፋም እምሽክ አድርጎ በልቶታል። እየተቃረበ ያለው ዓይነት የፌዝ ምርጫ ወያኔ እንደ እንጀራ የራበውን የተቀባይነት እጦት ለአጭር ጊዜ ያስታግስለት ይሆናል እንጂ የሀገሪቱን እያደር እየተወሳሰበ የመጣ ችግር ለጊዜውም እንኳን የሚያስታግስ አይሆንም፤ ይልቁንም ጊዜው በገፋ ቁጥር ችግሩ መቋጠሪያ የጠፋው እየሆነ ይሄዳል።

የሁኔታውን አሳሳቢነት ከግምት ውስጥ በማስገባት የአርበኞች ግንቦት 7: የአንድነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ አመራር የወቅቱን ...... ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )



## መልእክት ለወጣቶች፤ (በወጣቶች ጉዳይ መምርያ)

ወጣት ለአገር እድገትና ብልጽግና የሚያበረክተው አስተዋጾ ከፍተኛና በቀላሉ ለውጥ ማምጣት የሚችል ኃይል ያለው የህብረተሰብ ክፍል መሆኑ ይታወቃል። ይህን በቀላሉ ለውጥ ማምጣት የሚችል ትውልድ ጊዜው በሚጠይቀውና ለአገራችን በሚበጅ መልኩ ማደራጀት፣ መምራትና ንቅናቄው ለሚያደርገው የነጻነት፣ የፍትህና ዲሞክራሲ ትግል ግንባር ቀደም ሁኖ እንዲሰለፍ ማስቻል የንቅናቄያችን አርበኞች ግንቦት ሰባት ዋና ተግባር ነው። ስለሆነም ንቅናቄያችን ወጣቱ ትውልድ ለአገር እድገትና ዲሞክራሲያዊ ግንባታ የያበረከተው አስተዋጾ ከፍተኛና አስፈላጊ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የወጣቶች ጉዳይ መምሪያን አቋቁሞ ወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል ትግሉን እንዲቀላቀል በማድረግ ላይ ይገኛል።

መምርያው የተቋቋመበት ዋና ዓላማ ወጣቱ ትውልድ የወያኔን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ፣ ኢ-ዲሞክራሲ፣ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት እና የሚያራምደውን የዘር ፖለቲካ በአጠቃላይ የወያኔን አምባገነናዊ ስርዓት በሚገባ እንዲገነዘብ በማድረግ እንዲሁም የንቅናቄያችንን ዓላማና ግብ በማስረዳት ለነጻነት፣ ፍትህና ዲሞክራሲ ለሚደረገው የሁለገብ ትግል ወጣቱ ትውልድ ድርሻውን እንዲወጣ ማድረግ እና ኢትዮጵያ አገራችንን ጠብቆና አስከብሮ ለትውልድ የማስተላለፉን ኃላፊነት እንዲረከብ ማስቻል ነው።

እንደሚታወቀው የአንድ አገር ቀጣይነት ያለው እድገት የሚለካው በአላት መሠረተ ልማት፣ ቁሳዊ ሃብትና ንብረት ብቻ ሳይሆን በዋናነት ይህን ተረክቦ በአደራ ለትውልድ ማስተላለፍ የሚችል ትውልዳዊ ትስስር ሲኖር ነው። ይህንንም የአገርና የህዝብ አደራ ድልድይ ሆኖ ከትውልድ ወደ ቀጣዩ ትውልድ የሚያስተላልፍ ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ስለሆነ ኢትዮጵያን ከወያኔ የጨለማ ቡድን መታደግ ለነገ የማይባል አገራዊ ግዴታ መሆኑን ተገንዝቦ ወጣቱ ትውልድ ኃይሉንና አቅሙን ተጠቅሞ የእራሱን ነጻነት በእራሱ ማወጅ እንደሚችል መምርያው ያሳስባል።

በማንኛውም አገር፣ ጊዜና ዘመን እያንዳንዱ ትውልድ የአገሩ ወራሽ፣ ተተኪና ተረካቢ፣ ጠባቂና ለሚቀጥለውም ትውልድ የማውረስ፣ የማስተላለፍና የማስረከብ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት። ስለሆነም አገርን ከእነ ሙሉ ክብራ ለሚቀጥለው ትውልድ ማስተላለፍ የእኛ የወጣቶች የዜግነት ግዴታ መሆኑን ተረድተን ጥልቅ በሆነ አገራዊ ስሜት በሦስቱም ዘርፍ ማለትም በማህበራዊ፣ በምጣኔ ሃብታዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ አገራዊ ተጽዕኖ ማድረግ እንደሚቻል በእርግጠኝነት የወጣቶች ጉዳይ መምርያ በድጋሚ በአጽንኦት ያሳስባል።

## ውድ የአገራችን ወጣቶች ሆይ፤

የምንወዳትና የምንሳሳላት ብርቅዬ የጀግኖች አገር ኢትዮጵያ በባንዳዎች ወያኔ ለ24 ዓመታት የጥፋት ዘመቻ እየተካሄደና እየተፈጸመባት ሉዓላዊነቷ ተንቆ ተገኖአለች። አምባገነኑ የወያኔ ቡድን በጠበንጃ ኃይል ስልጣን ከያዘበት ጀምሮ ሰብአዊ መብታችን ተጥሶ፣ ዲሞክራሲያዊ መብት ተነፍጎን፣ ተፈጥሮአዊ መብታችን ተነጥቆ፣ የዜግነት ማንነታችን ባንዲራችን ሳይቀር ተቀይሮ፣ ብሔራዊ ሃብትና ንብረት እየተዘረፈ፣ የአገራችን አርሶ አደር ለም መሬቱ እየተሸጠ፣ እተነጠቀና እየተባረረ፣ ለአገር የሚታገለው ንጹህ ዜጋ ፀረ ሰላም ፀረ ህግ ፀረ መንግሥት በመባል የሽብርተኛ ሕግ ወጥቶለት እየታሰረ፣እየተገደለና እየሞተ፣ እየተፈናቀለና እየተሰደደ፣ በግፍና በጭቆና ላይ መሆኑን ለአንተ ንቁ ህልቢና ላለህ ወጣት ትውልድ የተሰወረ አይደለምና በጽኑ በአስቸኳይ ታገለው። ነጻነትን

አውጅ፤ ፍትህን ተቀዳጅ! ታሪክህን መልስ! ወያኔን ይብቃህ ከህዝብ ላይ ውረድ በለው። ...... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት የሕዝብ ወገንተኝነቱን የሚያሳይበት ወቅት አሁን ነው!

ዘረኛውና ፋሽስታዊው የህወሃት አገዛዝ የኢትዮጵያን መከላከያ ሠራዊት በዘርና በፓለቲካ ወገንተኝነት በመከፋፈል ሹመቱና ጥቅማ ጥቅሙን ለራሱ ወገን፣ ችግሩንና መከራዉን ግን ለሌላው ኢትዮጵያዊ ያደለ መሆኑ ይታወቃል። በዚህም መሠረት ሳይማሩና ሳይሰለጥኑ የጀኔራልነት ማዕረጎችን በሙሉ ሰብስበው የወሰዱት የህወሓት አባላት መሆናቸው የአደባባይ ሚስጢር ነው።

በወያኔ መዳፍ ውስጥ እየተሰቃየች ባለችው ኢትዮጵያችን ውስጥ በዘርም ይሁን በፓለቲካ አመለካከት ከህወሓት የተለዩ ኢትዮጵያዊያን ቢማሩም ቢሰለጥኑም ለከፍተኛ አመራርነት እንደማይበቁ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ያየነው ነው። አገዛዙ ቅራኔ ውስጥ በገባባቸው ቦታ ሁሉ እየዘመቱ ሕይወታቸውን እየገበሩ ያሉት ግን በመካከለኛና ዝቅተኛ ማዕረጎች ያሉ ኢትዮጵያዊያን መኮንኖችና ብዙሃኑ የሠራዊቱ አባላት የሆኑ ወታደሮችናቸው። ብዙሃኑ የሠራዊት ክፍል አለቆቹን ከመጠበቅ ባለፈ ድምጹን ከፍ አድርጎ ለመናገር እንኳን የማይፈቀድለት ሎሌ ተደርጓል።

ለኢትዮጵያዊ ወታደር ለህወሃት ሎሌ ከመሆን በላይ የሞት ሞት የለም። ብዙሃኑ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊቱ አባላት በጥቂት የወያኔ ሹማምንት የሚረገጥ መሆኑ የሠራዊቱን አባላት የግል ስብዕና ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የሠራዊቱን ክብር ይነካል። የሠራዊታችን የህወሓት አገልጋይ መሆን የምንወዳት አገራችን ኢትዮጵያን ያዋርዳል። ይህ ዉርደት በዚህ ሁኔታ መቀጠል የለበትም።

ከእንግዲህ ጄኔራሎችና ሌሎችም የበላይ አዛዦች ሁሉ የአንድ አካባቢ ተወላጆች በሆኑበት ሠራዊት ውስጥ ተስማምቶ መኖር መቀጠል እያንዳንዱን የመከላከያ ሠራዊት አባል ሊያሰፍር ይገባል። የህወሓት ጄኔራሎች ጮማ በውስኪ ሲያወራርዱ፤ በህንፃዎች ግንባታ፣ በባንኮች ንግድ፣ በግብርናና በኢንዱስትሪ ዘርፍ ተሰማርተው ቢዝነሳቸውን ሲያጧጥፉ፣ ምስኪኖቹ የሠራዊቱ አባላት በኦጋዴን፣ በአፋር፣ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላ፣ በአማራና በሌሎች የአገሪቱ ግዛቶች እየተወረወሩ ወገኖቻቸውን የሚፈጁበት ሥርዓት ማብቃት አለበት። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ብዙሃኑ አባላት ቤተሰቦቻቸው በችጋር እየተቆሉ የአዛዦቻቸው ሀብት ጠባቂ መሆናቸው ማክተም አለበት።

የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት የጭለማ ዘመን ታሪክ እያበቃ መሆኑን የሚጠቁሙ ምልክቶች እየታዩ ነው። መሣሪያዎቻቸውን እንደያዙ የነፃነት ኃይሎችን የሚቀላቀሉ የሠራዊቱ አባላት ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨረመ መጥቷል። ሠራዊቱ ከሕዝብ ጎን እንደሚቆም ውስጥ ውስጡን የሚላኩ መልዕክቶች እየተበራከቱ መጥተዋል። ይህ አበረታች ዜና ነው፤ ግን በቂ አይደለም። ወያኔን ከውስጥም ከውጭም የምናጣድፍበት ጊዜው አሁን ነው። የነፃነት ኃይሎችን መቀላቀያ ጊዜ አሁን ነው፤ በሠራዊቱ ውስጥም በህቡዕ መደራጃ ጊዜ አሁን ነው። ይህን ጊዜ መጠቀም ብልህነት ነው።

አርበኞች ግንቦት 7፡ የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ ጥቂት የህወሓት ጥጋበኞች በብዙሃኑ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ላይ የሚያደርሱት በደል ማብቃት አለበት ይላል። አርበኞች ግንቦት 7፡ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አባላት በሙስና የደለቡት፣ ትዕቢተኛና ጨካኝ መሪዎቻቸው ፍጹም ኢትዮጵያዊ ባህርይ የሌላቸው ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች እንደሆኑ በመረዳት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ክንዱን እንዲያነሳባቸው ጥሪ ያደርጋል። ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ሕዝብም የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አንድ ወጥ እንዳልሆነ እና በመካከለኛና ዝቅተኛ ደረጃ ያሉ መኮንኖችና አብዛኞዎቹ ወታደሮች የሕዝብ ወገን መሆናቸውን እንዲገነዘብ ያሳስባል። "አብረን ነው ዘረኛውና ፋሽስቱን ወያኔን ከኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ አውርደን የምንጥለው" ስንል አብዛኛው የመከላከያ ሠራዊታችን ኢትዮጵያዊ ወገናችን እንደሆነ እና በወደፊቷ ኢትዮጵያ ግንባታ ውስጥም ጉልህ ሚና እንዲጫወት የምንፈልግ መሆኑን ግልጽ ማድረግ እንሻለን። የመከላከያ ሠራዊቱም የሕዝብ ወገንተኝነቱ በተግባር እንዲያሳይ ጥሪ እናደርጋለን። የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት የሕዝብ አካል ነው፤ የሕዝብ ወገናዊነቱ በተግባር የሚያሳይበት ትክክለኛ ጊዜ ደግሞ አሁን ነው እንላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

---

## የ2007 ቱን ሀገራዊ ምርጫ ሂደት እና ከምርጫዉ ዉጭ ያሉ አዋጭ ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

የአገራችን የፓለቲካ ሁኔታ በጥንቃቄ መርምሮ የሚከተሉት ግንዛቤዎች ላይ ደርሷል።

1. ህወሓት ብዙዎች እትዮጵያዊያን የተሰውላቸውን አንድነት ፓርቲንና መኢአድን በመበተን የድርጅቶቹን ስምና ንብረት ለአገልጋዮቹ መስጠቱ፤ ከዚህ በፊት ሲያደርግ እንደነበረው የመራጭን ድምጽ መስረቅ ሳይበቃው የምርጫ ተወዳዳሪንም መዝረፍ መጀመሩን አመላካች ነው። ይህ ተግባር ህወሓት የምርጫ ውጤትን ብቻ ሳይሆን ተወዳዳሪዎችንም እሱ ራሱ ለመምረጥ መወሰኑን ያሳያል፤ ከዚህ በተጨማሪ የሴራ ምርጫውን ከጅምሩ ጀምሮ አስቀድሞ እስከተወሰነለት መዳረሻው ድረስ ለምንም ዓይነት ያልተጠበቀ አጋጣሚ (በምርጫው ወቅት የሚደረጉትን ክርክር ተብዬዎች ጨምሮ) እድል ላለመስጠት ወስኖ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን በግልጽ ያሳያል፤
2. ይህ እኩይ ውሳኔ በምርጫ ቦርድ ፊርማና አንደበት ቢነገርም ምንጩ የህወሓት ፓሊት ቢሮ መሆኑን የሚከተሉት ተግባራት ይጠቁማሉ፤
   - 2.1 በምርጫ ቦርድ በኩል እንዲገለጽ የተወሰነው እርምጃ ለማስመሰል ያክልም ቢሆን የህጋዊነት ሽፋን እንዲኖረው አለመደረጉ ውሳኔው ፍጹም እብሪተኛ በሆነ አካል መወሰኑን ያመለክታል። እንዲህ ዓይነቱ እብሪተኛ አካል ደግሞ የህወሓት ፓሊት ቢሮ ነው። ውሳኔውን ለማስፈፀም የነበረው ጥድፊያም ይህንኑ ያጠናክራል።
   - 2.2 ለማስመሰያ ያክል እንኳን ምንም አይነት የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳይኖር ፓሊስ የአንድነትና የመኢአድ ቢሮዎችን መውረሩ፤ ህወሓት አንድነትንና መኢአድን አጥፍቶ የድርጅቶቹን ስሞችና ንብረቶች ለሚፈልጋቸው ሰዎች ሰጥቶ በአስቸኳይ ለምርጫ ድራማው በፊት መስመር ሊያሰልፋቸው መወሰኑን አመላካች ነው። እንዲህ ዓይነት ከባድ ውሳኔ የሚሰጠው ደግሞ የህወሓት ፓሊት ቢሮ ብቻ ነው።
   - 2.3 ወደ ፈቃድ መንጠቅ ከመደረሱ በፊትም በሰማያዊ ፓርቲ፣ በአንድነትና በመኢአድ አባላት የደረሰው አረመኔያዊ ድብደባ፤ ንቁ የፓለቲካ ተሳትፎ የሚያደርጉ ዜጎች ላይ የሚደርሰው እስር፣ መሰወርና እና ባልታወቁ ሰዎች ተገድሎ መገኘት መብዛት እነዚህን አገራዊ ፓርቲዎች የመበተን የፓለቲካ ውሳኔ መሰጠቱን አመላካቾች ናቸው።
3. ለጊዜው የፈቃድ ነጠቃና የንብረት ዘረፋ የተፈፀመው በአንድነትና በመኢአድ ላይ ቢሆንም በሰማያዊ ፓርቲ ላይ በየእለቱ እየጠነከረ የመጣው የአፈና እርምጃም በተመሳሳይ ፓርቲውን ወደማገድ አለዚያም ፈጽሞ መንቀሳቀስ ወደማይችልበት ደረጃ ሊያደርሰው ይችላል የሚል እምነት አሳድሯል። ሌሎች ፓርቲዎችም ከዚህ ህወሓት ካሰመረው የውሸት ጫወታ መስመር የመውጣት ዝንባሌ ቢያሳዩ ተመሳሳይ እርምጃ አይቀርላቸውም።
4. የህወሓት የወቅቱ የጥፋት ዒላማ ያነጣጠረው አንፃራዊ በሆነ መንገድ የተሻለ መዋቅርና ማኅበራዊ መሠረት ባላቸው እና በአገራዊ አጀንዳዎቻቸው በሚታወቁ ፓርቲዎች ላይ መሆኑ፤ የወቅቱ የጥፋት ዘመቻ የኢትዮጵያ አንድነትን የማዳከምና ከፋፍሎ የመግዛት የህወሓት ትልቁ አጀንዳ አካል መሆኑን ያሳያል።
5. እራሱን በዘር ያደራጀዉና ኢትዮጲያ ዉስጥ ያለዉ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ አደረጃጀት ከዚሁ እሱ ከተደራጀበት የዘር አደረጃጀት ዉጭ እንዲሆን በፍጹም የማይፈቅደዉ የወያኔ አገዛዝ፤ መጣፊያው ሲያጥረውና ወደ ማይቀረው ውድቀቱ ሲያመራ፤ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል እንዳለችው አህያ አገራችን ኢትዮጵያን በቀላሉ ወደማትወጣዉ የዘዉግ ግጭት ዉስጥ አስገብቶ ዘመናት ያስቆጠረዉ አንድነቷ እንዲፈረስ በትጋት እየሠራ መሆኑን ያሳያል።
6. ከመለስ ዜናዊ ሞት ወዲህ ህወሓት ከሁሉን ጠቅላይ (totalitarian) አገዛዝ ወደ ፋሽስታዊ ቡድንነት ያሽቆለቆለ መሆኑን አርበኞች ግንቦት 7 ተገንዝቧል። ህወሓት ዘረኛ፣ ጠቅላይና ፈላጭ ቆራጭ ጨቋኝ በመሆኑ ፋሽስት ብለነዋል። ሆኖም በታሪክ የሚታወቁ ፋሺስታዊ አገዛዞች ከፍተኛ ብሄራዊ ስሜት የነበራቸው ሲሆን የህወሓት ፋሽስታዊ አገዛዝ ግን ብሔራው ስሜት አልባ መሆኑ ልዩ እና የበለጠ አደገኛ ያደርገዋል። ይህ ፋሽስታዊ ቡድን የህወሓት መሪዎችንና ጥቂት ሌሎች አጫፋሪዎቻቸውን የያዘ ለጊዜው አስተባባሪ መሪ የሌለው ሆኖም ግን የጦር ሠራዊትን፣ የስለላ መዋቅሩንና ፓሊስን ተቆጣጥሮ በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያን እየገዛ ያለው ይህ አስኳል የለሽ ፋሽስታዊ ቡድን መሆኑ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን አርበኞች ግንቦት 7 ተገንዝቧል። ይህ ፋሽስታዊ ቡድን ተደላድሎ መሪ እንዲፈጥር ከተፈቀደለት አገራችንን የከፋ መከራ ውስጥ ሊከታት እንደሚችል ግንዛቤ ተወስዷል።

ከላይ በአጭሩ ከተራ ቁጥ 1 እስከ 6 የተዘረዘሩትን በማገናዘብ በግንቦት 2007 ሊደረግ የታቀደውን አምስተኛው ዙር ሀገር አቀፍ የሴራ ምርጫን በተመለከተ የአርበኞች ግንቦት 7 አመራር ውሳኔዎችን አስተላልፎ ከዚህ የሚከተሉት ጥሪዎችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ አቅርቧል።

1. በምርጫ 2007 መሳተፍ ለዲሞክራሲያዊ ለውጥ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ይልቅ ፋሽስታዊውን ቡድን የሚያጠናክርና ...... ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

# ከህወሃት ምርጫ የሚገኘው ትርፍ ውርደት ብቻ ነው

ህወሃት ኢሕአዴግ የተባለውን ጭንብል አጥልቆ አገሪቷን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ሥር ካስገባ ግዜ ጀምሮ በኢትዮጵያዊያን ላይ የተፈፀሙ ወንጀሎች ፈርጀ ብዙ ናቸው። እነዚህ ፈርጀ ብዙ ወንጀሎች በልዩ ልዩ ተቋማት እና ግለሰቦች በማስረጃ ተደግፈው ተመዝግበው ተቀምጠዋል። ከሰሞኑ እንኳ በአውሮፓ ህብረት ውስጥ በተደረገው አንድ ጉባኤ ላይ ግራሃም ፔብል የተባሉ ታዋቂ ሰው ህወሃቶች የፈፀሟቸውን ወንጀሎች በማስረጃ አስደግፈው ከዘረዘሩ በኋላ ህወሃት *"አሸባሪ መንግስት"* ነው ብለዋል። ይሄ እውነት ነው። ኢትዮጵያ ከአምባገነን ገዥዎች ተላቃ የምታውቅ አገር አለመሆኗ የታወቀ ቢሆንም እንደ ህወሃት ያለ የህዝብ ጠላት መሆንን መርጦ የገዛ ህዝቡን የሚያሸብር መንግስት ነኝ የሚል አካል ግን አልታየም።

ህወሃት አሸባሪ ነው። ይሄ አሸባሪ ቡድን በሚያካሂደው ምርጫ ውስጥ የተሳተፈ ሁሉ እድል ፈንታው ውርደት፤ እስራት፤ ስደት እና ግዲያ መሆኑን እስከ ዛሬ በተካሄዱት ምርጫዎች አይተናል። ህወሃት ኢሕአዴግ የተባለውን ጭንብል አጥልቆ በምርጫ ሰበብ የብዙ ንፁህን ዜጎችን ደም አፍስሷል። በምርጫ ሰበብ ያፈረሰው ቤት፤ የበተነው ቤተሰብ ብዙ ነው። አገራችን በፖለቲካ እስረኞች ብዛት አቻ ያልተገኘላት ሁናለች። በስደተኛ ብዛትም የመሪነቱን ደረጃ ይዛለች። ይህን ሁሉ ግፍ ያዩ የውጭ ታዛቢዎች ኢትዮጵያን ከውዳቂ አገራት መካከል መድበዋታል።

ህወሃቶች በታሪክ አጋጣሚ ከተቆናጠጡበት ወንበር ከሚወርዱ ሞታቸውን እንደሚመርጡ ደጋግመው በአደባባይ ተናግረዋል። ለዚህም እነርሱ ምክንያት የሚሉት ይህን ወንበር ያገኘነው በደማችን ነው። በደም ያገኘነውንም ወንበር እንዲሁ የምናስረክብ አይደለንም ይላሉ። ወንበሩን አንለቅም ብለው ቢያቆሙ መልካም ነበር፤ ወንበሩን የምንለቅ ከሆነ አገሪቷን እንበትናታለን የሚለውን ነውር ሃሳብ ማቀንቀናቸው ደግሞ ህወሃቶቹ አንዳች ዓይነት የአዕምሮ ቀውስ ውስጥ መግባታቸውን ያመለክታል። የእነዚህን ቡድኖች ነውረኛነት በ1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ደህና አድርገን ታዝበናል። በሌብነት እና በሌላ ነውር ምክንያት ከድርጅቱ የተባረሩት ሳይቀሩ ተሰባስበው ህወሃትን ለማዳን የሚል የጥፋት ዘመቻ በአገሪቷ ላይ መክፈታቸው የሚረሳ አይደለም። ህወሃት ወንበሩን የሚለቅ ከሆነ ተመልሰን ወደ ጫካ እንገባለን ማለታቸው የአደባባይ ሚስጢር መሆኑም የሚረሳ አይደለም።

እስከ አሁን በተደረገው ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ ያተረፈው ነገር ቢኖር ውርደት እንጂ ክብር አይደለም። ህወሃቶች ምርጫ እያሉ ህዝቡን እያዋረዱ፤ የአገሪቷንም ሃብት እየበዘበዙ፤ እነርሱ ከህግ በላይ ሌላው ከእነርሱ ጫማ ስር ሁኖ የሚኖርበትን ሥርዓት እየሰሩ ኑረዋል። ይህ እነርሱ ለእነርሱ የሠሩት ሥርዓት እንዲሁ እንዲለወጥ ይፈልጋሉ ብሎ ከማሰብ የምናተርፈው ነገር ቢኖር ውርደት ብቻ ነው። ህወሃቶች የተፈጠሩበትም ምክንያት አገሪቷንና ህዝቧን ለማዋረድ ነው ለማለት የሚያስችሉን ከበቂ በላይ ምክንያቶች አሉ።

ህወሃቶች እንደ ጤነኛ ሰው ለማሰብ የሚያስችላቸው ስብዕና የሌላቸው መሆኑ ይታወቃል። እኛ ከስልጣን የምንወርድ ከሆነ አገሪቷን እንበትናታለን በሚል ቅዥት ውስጥ የመገኘታቸው ምስጢርም የስብዕናቸውን የዝቅጠት ደረጃ የሚያመላክት ነው።በሰላማዊ መንገድ ተወዳድረው እና ተመርጠው ስልጣን ለመያዝ በጎ ራዕይ ያላቸውን ሁሉ በጠላትነት ፈርጀው እና የአሸባሪነት ካባ ደርበውላቸው በጎ ራዕያቸውን እያመከኑ እንደሆነ እያየን ነው። አሁን በአንድነት እና በመኢህአድ ላይ የተወሰደው እርምጃ የዜጎችን በጎ ራዕይ የማምከን ተግባር መገለጫ ሁኖ ሊጠቀስ ይችላል። ህወሃቶች ራዕይ አልባ ናቸው።ለኢትዮጵያ በጎ ራዕይ ቢኖራቸው ኑሮ "እኛ ከሌለን አገሪቷን እንበትናታለን" አይሉም ነበር። ራዕይ ያለው ከእኔ የተሻለ ካለ ይሥራ ይላል እንጂ እኔ ካልሆንኩ ሞቼ እገኛለሁ አይልም። ህወሃቶች ቅዥታቸውን ራዕይ ብለው ይጠራሉ። በቅዥት ዓለም ውስጥም እንደሚኖሩ የሚነገራቸው ከተገኘም ዘራፍ ብለው አሸባሪ ይላሉ እንጂ ለማድመጥ ችሎታ እና ትዕግስት የላቸውም።

እንግዲህ ህወሃቶች ኢሕአዴግ የተባለውን የምናምንቴዎችን ስብሰብ ጭንብል አጥልቀው በሚያካሂዱት ምርጫ ላይ የተሳተፈ ሁሉ ያተረፈው ውርደት መሆኑን እናውቃለን። ይሄን ውርደት መምረጥ ትክክለኛ ምርጫ ሊሆን አይችልም። ህወሃት የያዘው ስልጣን የነብር ጭራ ሁኖበታል። የነብሩን ጭራ ከለቀኩ ደግሞ እጠፋለሁ የሚል ፍርሃት ውስጥ ወድቋል። ከዚህ ውድቀት ለመነሳት የሚያስችል እውቀትና ቅንነት ስለሌለው ጥላው እያስበረገገው መኖር ግድ ሁኖበታል። ይሄ በርጋጋ ቡድን በኢትዮጵያዊያን ላይ የፈፀመው ወንጀል በሰላማዊ መንገድ በሚደረግ ምርጫ ስልጣኑን እንዲለቅ ያደርገዋል የሚል እምነት የለንም። ይሄ ቡድን ካፈጣጠሩ ጀምሮ ቂመኛና ምህረትን የማያውቅ በመሆኑ ሌሎችንም የሚያየው ራሱን በሚያየው ዓይኑ ነው። ይሄ ቡድን ከራሱ ከበብ ወጥቶ በተለየ እና በተሻለ ሁኔታ ለማሰብ ቅንነት ስለሌለው ሁሉም ሰው እርሱ ራሱን ይመስለዋል። ይሄ ቡድን በዚህ መንፈስ ሁኖ በሚያካሂደው ምርጫ ውስጥ መሳተፍ ትክክለኛ አካሄድ ስለማይሆን ምርጫውን ህወሃትን ከመሠረቱ ለመቀየር መጠቀም ተገቢ አካሄድ ይሆናል። ምርጫው ህወሃትን ከሥሩ የማይቀይረው ከሆነ ይህ ዘረኛና ዘራፊ ቡድን ለሌሎች ማሳየት የሚፈልገውን ህጋዊ ሽፋን በማግኘት በጥፋት ጎዳናው እንዲቆይ ያደርገዋል።

የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ !

ህወሃቶች አገሪቷን ከተቆጣጠሩ ዘመን ጀምሮ ከተደረጉት ምርጫዎች ያተርፍከው ውርደት ነው። ህወሃቶች ምርጫ እያካሄዱ ልጆችህን ይቀጠቅጣሉ፤ ይገድላሉ። ምርጫ ብለው ሲያበቁ አልመረጥከኝም ብለው መሬትህን ይነጥቃሉ፤ ከአቅምህ በላይ ግብር ይጥሉብሃል። ናና ምረጥ ብለው ሲያበቁ አልመረጥከኝም ብለው ከሥራህ ያባርሩሃል፤ ቤተሰቦችህንም ይበትናሉ። ህወሃቶች ምርጫ በሚሉት ቧልት የደረሰብህ ውርደት ብዙ ነው። እንግዲህ በህወሃቶች ምርጫ የምትሳተፍ ከሆነ እስከ ዛሬ ሲፈፀም የቆየውን ውርደት ለመጨረሻ ግዜ በቃ ልትለው ቆርጠህ ተነሳ። ህወሃቶች የኢትዮጵያ ጠላት መሆንን የመረጡ ቡድኖች ናቸው።የራስህን ጠላት በራስህ ላይ መርጠህ እንዳትሾም ለራስህ ተጠንቀቅ።

እኛ አርበኞች-ግንቦት ሰባት የአንድነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ህወሃት በሰለጠነ መንገድ በሚደረግ የፖለቲካ ውድድር ውስጥ ገብቶ ለመፎካከር ችሎታ እንደሌለው አይተናል። ችሎታ ብቻ ሳይሆን ቅንነትም የሌለው ክፉ ቡድን መሆኑንም እናውቃለን። ህወሃት የጨበጥኩትን ስልጣን የምለቀው "በሬሳየ ላይ ነው" ያለው ሃሳብ የያዝነውን የትግል መንገድ እንድንመርጥ አድርጎናል። ህወሃትም "ሞት ወይም ስልጣን ላይ መቆየት" የሚል የማይናወፅ እምነቱ እንዲሁ በዋዛ እንደማይቀየር አበክሮ ነግሮናል። እነዚህ ቡድኖች በጎ የሆነ አገራዊ ራዕይ ኑሯቸው እና የዜጎችን ብሄራዊ ስሜት አጠናክረው አገሪቷን በአንድነት ለመምራት በጎ ምኞት ቢኖራቸው ኑሮ በስልጣን ላይ ለመቆየት ቢሚገቱ ግድ ባላላን ነበር። እነርሱ ግን አገር እያፈረሱ፤ በየእለቱ የንፁህ ዜጋ ደም እያፈሰሱ፤ ወጣቱን ለስደት እየዳረጉ፤ ገበሬውን መሬት አልባ አድርገው የአረብና የህንድ ባሪያ እያደረጉት፤ ቀና ብሎ ያያቸውን ሁሉ አሸባሪ እያሉ ለእስር እየዳረጉ፤ ብዙ ዜጎችን አገር አልባ አድርገው እያየን ዝም ለማለት ሰው መሆናችን አይፈቅድልንም። በሚገባቸው ቋንቋ ልናናግራቸው ተዘጋጅተናል። ብዙ ወጣቶች ከመላው የአገሪቷ ክፍሎች ህወሃቶች የገነቡትን የዘረኝነት አጥር እያፈረሱ ወደ ትግሉ እየተቀላቀሉ ነው። በእኛ ዘንድ ማንነታችን ኢትዮጵያዊነት እንጂ ሌላ መሰፍረት አይደለም። ኢትዮጵያዊነት በቀይ ቀለም በልባችን ውስጥ የተቀረፀ የምንሰዋለት ማህተማችን ሁኗል።

በህወሃት ዘመን ስሟ የጎደፈው ኢትዮጵያችንን ስሟን በደማቅ ብዕር ልንፅፍ ተነስተናል። ኢትዮጵያን ወደ ቀደመው ክብሯ ልንመልሳት አያቶቻችን በተመላለሱበት ተራራ ላይ ተሰማርተናል። ኢትዮጵያችን እንደ ነብር የተዋበ ኽንጉርጉርነቷን እንደያዘች የታፈረች አገር ሁና ስሟ እንዲነሳ ለማድረግ የሚያስችለንን የትግል ስልት መርጠናል። ወጣቶቿ የማይሰደዱባት፤ዜጎቿ በልተው የሚያድሩባት፤ ምሁራኖቿ እውቀታቸውን ያለ ገደብ የሚያፈሱባት፤ ነጋዴዎች ያለ ፍርሃት ነግደው የሚያተርፉባት፤ አዛውንቶች የሚጦሩባት፤ ህፃናት በደስታ የሚቧርቁባት፤ ገበሬው መሬት አልባ የማይሆንባት፤ ጋዜጠኛው ከሂሊናው ተስማምቶ ለሙያው ብቻ ታማኝ ሁኖ የሚኖርባት፤ ኪነ-ጥበብ የአደርባዮች መናኸሪያ ከመሆን ወጥታ አደርባዮችን ለመገሰፅ የምትችልበት፤ ዜጎቿ ያለ ፍርሃት የሚኖሩባት፤ ፍፁም ሠላም የሰፈነባት፤ በአጠቃላይ እግዚአብሄር አገሩ ኢትዮጵያ ነች ተብላ የምትታወቅ አገር ለመፈጠር ቆርጠን ተነስተናል። በዚህ መሠረትነት የጀመርነው ትግል ዕለት ዕለት እያማገበት፤ እየተጠናከረ እና እየገለበተ እየሄደ ነው። ካሁን በኋላ ህወሃትን ከስልጣን ለማስወገድ ግዜውን የምንመርጠው እኛ እንጂ ማንም አይሆንም። ግዜው በደረሰ ግዜ አገራችንን እና ዜጎቿን ያዋረዱ በሙሉ ወየውላቸው። ከእኩይ አስተሳሰባቸው አንመለስም ያሉ በሙሉ የመጥፊያ ጉድጓዳቸውን እየማሱ እንደሆነ ስንነግራቸው ከክፉ አስተሳሰባቸው ለመመለስ አሁንም ቢሆን እንዳልዘገየ ልናስታውሳቸው እንወዳለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!

## ሚስተር ግርሃም ፒብልስ ለአውሮፓ ህብረት የተናገሩት ንግግር ወያኔን አስቆጣ

በቤልጂም ዋና ከተማ ብራስልስ በተዘጋጀው ኮንፍረንስ ላይ ተጋባዥ የነበሩት የክርኤት ትረስት ዳይሬክተር የሆኑት ሚስተር ግርሃም ፒብልስ በኢትዮጵያ ለሁለት አመታት ማለትም እ.ኤ.አ በ 2013 እና በ2014 በነበራቸው ቆይታ በሰብአዊ መብቶች አከባበር እና በዲሞክራሲ እሴቶች ላይ ያደረጉት ሰፊ ጥናት ተንተርሰው በስልጣን ላይ የሚገኘው የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ሽብርተኛ ነው ሲሉ ለአውሮፓ ህብረት ባቀረቡት ሪፖርት ተናግረዋል። ሚስተር ግርሃም በኢትዮጵያ በነበራቸው ቆይታ በተለይ በኦጋዴን አካባቢ ሰፊ ጥናት ማድረጋቸውን በመግለጽ በኢትዮጵያ ሰፊ የኦጋዴን አካባቢን ጨምሮ በመላ አገሪቱ ማለትም በኦሮሚያ፤ አማራ፤ ጋምቤላና በሌሎችም አካባቢዎች ሽብርተኝነት እየተፈጸመ ይገኛል ሲሉ ለህብረቱ አስረድተዋል። ሚስተር ግርሃም አያይዘውም የሽብር ወንጀሉ እየተፈጸመ የሚገኘው በፋሺስቱ ወያኔ ዓገዛዝ መሆኑን በሁለት አመታት ቆይታቸው የተመለከተቱትን በማስረጃነት በማጣቀስ ለህብረቱ ተናግረዋል።

በስልጣን ላይ የሚገኘው አገዛዝ ሹማምንትና ቅጥረኞች ስለ ህግ የበላይነት፤ ስለ ዲሞክራሲና የሰብአዊ መብት አያያዝ ያውሩ እንጂ አንዱንም ተፈፃሚ እያደረጉ አለመሆኑን አረጋግጫለሁ። በኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ የለም፤ ነፃ ሚዲያ የለም፤ ዲሞክራሲ የለም ስለዚህ የአውሮፓ ህብረትም ሆኑ ሌሎች ሃያላን አገሮች በተለይ መጭውን ምርጫ ለመታዘብ መሄድ የለባቸውም ሲሉ ሚስተር ግርሃም ጠይቀዋል።

በመላ አገሪቱ በአገዛዙ አስፈፃሚነት በቅጥረኛ ወታደሮችና የአካባቢ ሚሊሻዎች አማካኝነት የአስገድዶ መድፈር፤ ግድያ፤ ማሰቃየት (ቶርቸር) ወንጀሎች በስፋት እየተፈጸመ ይገኛል ያሉት ሚስተር ግርሃም ችግሩ በኦጋዴን አካባቢ እጅግ የከፋ መሆኑን ለህብረቱ ተናግረዋል። በተለይ በኦጋዴን የአገዛዙ ቅጥረኛ ወታደሮችና ሚሊሻዎች በአካባቢው ሴቶች ላይ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እየፈጸሙ እንደሚገኙ በመግለጽ ፋሽስታዊው አገዛዝ በአካባቢው የጦር ካምፖች ውስጥ ሴት ልጅን አስገድደው መድፈር በተመለከተ እንዲሁም የሴትን ልጅ ክብረ ንጽህና እንዴት መገርሰስ እንደሚቻል ለወታደሮችና ለሚሊሻዎች ስልጠና እንደሚሰጣቸው ወታደሮችንና ሚሊሻዎችን ጠይቀው ማረጋገጥ መቻላቸውን ለህብረቱ አስረድተዋል። በዚህ ግፍ የተነሳ ብዙ ቁጥር ያላቸው የአካባቢው ሴቶች በሚደርስባቸው የአስገድዶ መደፈር ወንጀል ከዕለት ዕለት ለሞት እየተዳረጉ እንደሚገኙ በአይን መመልከታቸውን ተናግረዋል። የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በኦጋዴን አካባቢ ነዋሪዎች ላይ የተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችንና ሰቆቃዎችን እየፈጸመ የሚገኘው ዜጎች አገዛዙን በመፍራት ONLF የተባለውን ድርጅት እንዳይደግፉ ለማድረግ በሚል እንደሆነ ማረጋገጡንም ሚስተር ግርሃም ተናግረዋል።

በመጨረሻም ሚስተር ግርሃም ኢትዮጵያን እየመራ የሚገኘው መንግስት ሳይሆን ጨካኝ አምባገነን አገዛዝ መሆኑን በመጥቀስ በተለይ እንግሊዝ እና አሜሪካ ችግሩን ለመቅረፍ ምንም አልሰሩም ሲሉ ወቅሰዋል። እንግሊዝ፤ አሜሪካና የአውሮፓ ህብረት አገራት ኢትዮጵያን በተመለከተ የታወሩ አይኖቻቸውን በማብራትና እና የተዘጉ ጆሮዎቻቸውን በመክፈት በብዙ አስር ሚሊዮኖች የሚገመቱ ኢትዮጵያኖችን ስቃይና ሰቆቃ እንዲመለከቱና አፋጣኝ ምላሽ መስጠት እንዲጀምሩ አሳስበዋል። አለማቀፍ መንግስታት ከአገዛዙ ጎን መሰለፋቸውን በማቆም በህዝብ ጎን በመሰለፍ የሞራል ግዴታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል ሲሉ አበክረው አሳስበዋል።

## አሜሪካ መንግስት ለኢትዮጵያ የምትሰጠዉ እርዳታ ከዲሞክራሲና ከመብት አንፃር እንዲፈትሽ የዋሽግተን ፓዎስት ጋዜጣ ጠየቀ

*በኢትዮጵያ ያለው ፋሺስታዊ አገዛዝ ከኢራን መንግስት በመቀጠል በዜጎች ላይ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የሚያካሂድ አምባገነን ስርአት መሆኑም በርዕሰ አንቀጹ ተመልክቷል*

በፌብሩዋሪ 8 ቀን 2015 ኢ.ም ታትሞ ለንባብ የበቃው በአለማቀፍ ደርጃ ሰፊ ተነባቢብነትና ታአማኒነትን ያተረፈው የዋንግተን ፓዎስት ጋዜጣ በርዕሰ አንቀጹ ይዞት በወጣው ጽሁፉ አሜሪካ ጨምሮ ሌሎች ሐያላን አገሮች ለኢትዮጵያ እያደረጉት የሚገኙትን ሰፊ ድጋፍና እርዳታ አበክረው እንዲያጤኑ አሳስቧል።

የሂውማን ዎችስ ሪፓርትን እና የኮሜቴ ቱ ፕሮቴክት ጆርናሊስትስ አለማቀፍ ድርጅቶችን በማስረጃነት ያቀረበው ዋሽንግተን ፖስት በኢትዮጵያ ባለው አፋኝ አገዛዝ ከ 2010 ጀምሮ ከ 60 በላይ ጋዜጠኞች ለስደት መዳረጋቸውንና ከ19 ያላነሱት ደግሞ ለእስር መዳረጋቸውን እንዲሁም 22 ጋዜጠኞች የወንጀለኝነት ክስ እንደተመሰረተባቸው አመልክቷል።

የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዙን የሚተቹ ጽሁፎችን በሚጽፉ ጋዜጠኞች ስልክን ጨምሮ በኢሜል ማስፈራሪያዎች ከ አገዛዙ ሹማምንትና የደህንነት አካላት እንደሚደርሳቸውና በኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ከወጭ አገራት የሙያ አጋሮቻቸው ጋር ሆነ ከአለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ፈጥረ ቢገኙ ለእስር እንደሚዳረጉ የተመለከተ ሲሆን ፋሺስታዊው አገዛዝ የተሰደዱ ጋዜጠኞችን ከጎረቤት አገሮች ጭምር እንደሚያሳፍንና የተለያዩ ድህረ ገፆችንና ሚዲያዎችን የማፈን ስራ እንደሚሰራ ተመልክቷል።

መጭውን ምርጫ ተከትሎ ብርክ ውስጥ የገባው የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከ 5 በላይ የግል ጋዜጠኞችንና መፅሄቶችን መዘጋታቸውን በመግለጽ የተገለጸ ሴንሰርሽፕና የፕሬስ አፈና ከሚቹ መለስ ዜናዊ በኋላም የበተተካው አሻንጉሊቱ ሃይልማርያም ደሳለኝ አስተዳደር እጅግ በከፋ ሁኔታ መቀጠሉ በጋዜጣው ተገልጿል።

ፕሬስንና ጋዜጠኝነትን በተመለከተ ከጎረቤት አገር ኤርትራ ጋር ኢትዮጵያን በንፅፅር ለማሳያነት ያቀረበው ዋሽንግተን ፖስት ኤርትራ በርካታ የታሰሩ ጋዜጠኞችን መልቀቋን በመጠቆም ከኢትዮጵያ እጅግ በተሻለ ሁኔታ ላይ እንደምትገኝ ገልጿል።

በመጨረሻም ጋዜጣው ኢትዮጵያ ከአሜሪካ መንግስት ከፍተኛ እርዳታ ከሚጋብሱ አገራት አንዷ መሆኑዋን በማስረጃዎች በማስደገፍ ያቀረበ ሲሆን የኦባማ አስተዳደር የሚሰጠውን እርዳታና ድጋፍ በአገሪቱ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እጅግ በከፋ ሁኔታ እያሽቀለቀለ ከሄደው የሰብአዊ መብት አያያዝና የዲሞክራሲ እጦት አንፃር እንዲፈትሽ አሳስቧል። ጋዜጣው በማያያዝም በአገዛዙ የፈጠራ ክስ ተወንጅለው ለእስር የተዳረጉ ጋዜጠኞች እንዲፈቱ የአሜሪካ አስተዳደር ጫና ማሳረፍ አለበት ብሏል። ምዕራባውያን አገራትም ጋዜጠኞችን በፈጠራ ክስ ለእስር እየዳረገ ከፍተኛ ሰቆቃና የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እየፈጸ ለሚገኝ አገዛዝ የሚያደርጉትን ድጋፍም ሆነ እርዳታ ማቆም አለባቸው ሲል ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ አሳስቧል።

## የ2007 ቱን ሀገራዊ ምርጫ ሂደት እና ከምርጫዉ ዉጭ ያሉ አዋጭ ... ( ከገጽ 2 የዞረ )

2. የኢትዮጵያን ሕዝብ የወደፊት ዕድል የሚገድል በመሆኑ፣ ለፍትህ፣ ለነፃነት፤ ለዲሞክራሲና ለአገር አንድነት ግድ ያላቸው ወገኖች ሁሉ ከአሁኑ ከዚህ የይስሙላ ምርጫ ዉጭ ዓይኖቻቸውንና ሙሉ ጉልበታቸዉን በሌሎች የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃነት በሚያፋጥኑ አማራጮች ላይ እንዲያሳርፉ ጥሪ ያደርጋል። አርበኞች ግንቦት 7 የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ ዓይን ያወጣ የሴራ ምርጫ ይልቅ መብቱን፤ ነፃነቱንና እኩልነቱን በሚያፋጥኑለት በሕዝባዊ እምቢተኝነትና በሕዝባዊ አመፅ የትግል አመራጮች ላይ እንዲሳተፍ ለመላው ያገሪቱ ሕዝብ ጥሪ ያስተላልፋል። ህወሓት ማኅበረሰባችንን ለመከፋፈልና ለማባላት የሚያደርገውን እኩይ ሴራ በጋራ እንድናከሽፈው ወገናዊ ጥሪ ያስተላልፋል፤ "አንከፋፈልም፤ ተከፋፍለንም አንጠቃም" እንበል ይላል።
3. ህወሓትን ማስወገድ የሚቻለው በሕዝባዊ እምቢተኝነትና በሕዝባዊ አመጽ በመሆኑ፤ ከሁለቱ አንዱንም አለመያዝ ሌላ ሰው ታግሎ ነፃነቴን ያቀዳጀኝ እንደማለት የሚቆጠር በመሆኑ፤ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በአፋጣኝ ከእነዚህ ሁለት የትግል ዘርፎች ዉስጥ የተሻለ አስተዋጽኦ አበረክታለሁ በሚለው የትግል ዘርፍ ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርግ ጥሪ ያቀርባል።
4. አርበኞች ግንቦት 7፣ በሁለቱም የትግል ዘርፎች ድርጅታዊ መዋቅሩን እያሰፋና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር በሕዝባዊ እምቢተኝነትና በሕዝባዊ አመጽ ህወሓትን ከስልጣን ለማስወገድ አቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ በመሆኑ ኢትዮጵያዊያን በስፋት እንዲቀላቀሉት፤ በኅብረት እንድንቆም እና የህወሓትን ውድቀትና የኢትዮጵያን ትንሳኤ እንድናፋጥን ጥሪ ያደርጋል።
5. ያለንን አቅም በሙሉ ህወሓትን በማስወገድ ላይ ካዋልነው አንድ ጠንክር ያለ ሕዝባዊ አመጽ አገዛዙን ሊያፍረክርከው የሚችል በመሆኑ፤ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ከምርጫ ጋር ለተያያዙ ሥራዎች ሊውል ታስቦ የነበረው የሰው ኃይል፣ ጊዜ፣ ገንዘብና እውቀት ለሕዝባዊ አብዮት መቀስቀሻነት እንዲውል ጥሪ ያደርጋል።
6. በውጭ አገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንም በ2007 ምርጫ ላይ ጊዜና ንብረት ከማባከን ይልቅ በአንድ ልብ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሕዝባዊ አብዮት መቀስቀስ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ጥሪ ያደርጋል። ከሁሉም ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች የተውጣጣ አካል የዚህን ጥሪ ተፈፃሚነት እንዲከታተል ቢደረግ ይበልጥ ውጤታማ ይሆናል ብሎ ያምናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !**

**አርበኞች ግንቦት 7: የአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ**

**ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ**

**የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ -ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## **መልእክት ለወጣቶች፤ (በወጣቶች ጉዳይ መምርያ)**

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

***ውድ የአገራችን ወጣቶች ሆይ፤***

አገራችን ኢትዮጵያ ለብዙ ሺህ ዘመናት በነፃነት በቀደሙ አባቶቻችን ተጠብቃ የቆየችው በአካልና በደም ዋጋ ነው። በዚህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቆራጥነትና ፅናት አገርን በነፃነት መጠበቅ በዓለም ፊት ትልቅ ምሳሌነትን ያተረፈ፣ ዛሬ ለአለነውና ለመጭውም ትውልድ የሚኰራበት ሕያው የታሪክ አለኝታ፣ መመኪና ክብር ያለን ውድ ህዝቦች ነን። ይህ አኩሪ ታሪክ ፣ የዘላለም ሃብታችን በመሆኑ ጠብቀንና አስከብረን ለትውልድ ለማስረከብ ኃላፊነቱ በዋናነት የእኛ ወጣቱ ነው። ይህን እውነታ ተቀብሎ አገርን በነፃነት ለመጠበቅ ደፋ ቀና ከሚሉ ኢትዮጵያውያን ጋር አገራዊ ኃላፊነትንና ግዴታን ለመወጣት ዝግጁና ብቁ ሆኖ መታገል በእጅጉ ያስፈልጋል። ስለዚህ የአገራችን ወጣት ሁላችሁ ሰላም፣ ነጻነት፣ ፍትህና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመገንባትና አገራዊ ድርሻንም ለመወጣት በህብረት ተነስ፣ ታጠቅ፣ ሰው ሁን! ታሪክህን መልስ! አረመኔው ወያኔን በቃህ በለው!

በአጠቃላይ እኛ ወጣቶች ለአገር ነጻነት፣ ፍትህና ዲሞክራሲ ለሚደረገው ትግል የወጣትነትን አቅምና ኃይል ተጠቅመን የታሪክ ባለቤት እንሆን ዘንድ በሁለገብ ትግል የኢትዮጵያን ጠላት ወያኔን ለማስወገድ ከሚታገለው አርበኞች ግንቦት ሰባት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ጋር በመቆም ሰላም፣ ነጻነት፣ ፍትህና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያን ለመገንባት እና በጽናት አረመኔው ወያኔን ከህዝባችን ጫንቃ ላይ ለማስወገድ የበኩላችንን ኃላፊነትና ግዴታ መወጣት አለብን።

እንዲሁም አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን አገራችን የጣለችብንንና የሚጠበቅብንን አገራዊ ኃላፊነት በትጋትና በንቃት መወጣት የሁላችንም ግዴታ መሆኑን ተገንዝበን ለአገር እድገት የጀርባ አጥንት የሆነውን የህብረተሰብ ክፍል ወጣቱን ከወያኔ ትውልድ ገዳይና አገር ሻጭ አገዛዝ መታደግ ተቀዳሚ ተግባር በማድረግ ትግላችንን ይበልጥ ማጠናከር እንዳለብን በጥብቅ ለማሳሰብ እንወዳለን።

ወጣቱ ትውልድ ጊዜውን፣ ኃይሉን፣አቅሙንና ጉልበቱን ተጠቅሞ ለአገርና ለእራሱ ነጻነት እንዲታገል ምቹ ሁኔታወችን መፍጠር፣ ወኔና አገራዊ ስሜት እንዲኖረው መቀስቀስ፣ ወጣቱ ትውልድ በንቃትና በቁርጠኝነት ትግሉን በባለቤትነት ተረክቦ የድልና የነጻነት ዓርማ እንዲያውለበልብ ማድረግና ጥቅሙንም ማስገንዘብ የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል አገራዊ ተግባርና ኃላፊነት መሆኑን ተገንዝበን ሁላችንም ወጣቱን ትውልድ ከወያኔ ለመታደግ የድርሻችንን መወጣት ይኖርብናል።

በመጨረሻም ዘመኑ በአፈራቸው የብዙኃን መገናኛ መንገዶች በመጠቀም ለወጣቶች ወጣት ተኮር መልክቶችን በቀጣይነት ማስተላለፈ ስለተፈለገ በማነኛውም መንገድ ወጣቱን ለትግል ሊያነቃቃና አገራዊ እውቀት ሊያስጨብጥ የሚችል ግብዓት በመስጠት ትውልድ የማዳንና የማፍራት ተልእኮን እንድትጋሩ የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ መልእክቱን በአክብሮት ያስተላልፋል።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

የአርበኞች ግንቦት 7 ወጣቶች ጉዳይ መምርያ